# ይድረስ ለፕሮፌሰር

(ከአብርሃም  በየነ)

ይሉኝታን እንዳያይ አይን አንገት አዙሮ፣

በልጅነት እድሜው ከማን ምን ተምሮ፣

ሰው ለመሆን ቻለ ዳበረ አንደበቱ፣

አሳዳጊው በዳይ እናተና አባቱ፣

እንዲሉ ሆኖብን ልጅ እንዳሳዳጊው፣

ግብረ_ባህሪዎን ስንገመግመው፣

ነውርዎን እንዳያውቁ ይሉኝታ እንዲረሱ፣

ማን አሳደገዎ ከማን ምን ወረሱ?

ማተብ አልባው ምሁር ክቡር ፕሮፌሰር፣

ስለውነት ሰላገር እስኪ እንነጋገር፣

ማነው ተጠያቂ ማን ነበረ ገዳይ፣

ማንስ ነበር አጥቂ ማንስ ተከላካይ፣

ማን ነበር ግፈኛው ማን ነበር ተበዳይ፣

ማን ነበር ገራፊ ማን ነበር ታሳሪ፣

ማንስ ነበር ያኔ የደርግ አማካሪ?

ክብሩ ተሰርዞ የድሜ ጸጋው ውበት፣

ምንም ባይታደል ቢሆን የንጩት ሸበት፣

የበላ ባይ ምላስ ያድር ባይ አንደበት፣

ይሉኝታ ከድቶት ወይ አዙሮ ማየት፣

ቢሆን የክህደት ቃል የሃሰት ምስክር፣

እውነቱን ለማጠፋት በዚያች አገር ምድር፣



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ገዳይ ከሳሽ ሆኖ አጌጉል ክርክር፣

ፍትህና ርትህ በጠፉበት ምድር፣

እውነትን ፍለጋ ወርድና ቁመቷን፣

መርዶዋን ለመስማት የግፍ አማሟቷን፣

እንዲሉ ሆኖብን ጊዜ ነው ባለ ድል፣

ሺህ ምሁር በማጥፋት ሺህ ወጣት በመግደል፣

እጁ ደም የዋጀው ወንጀለኛው ሳለ፣

የተገላቢጦሽ ሟች ተወነጀለ !!

ሟቹን ወንጀለኛ ገዳዩን ተበዳይ፣

አድርጎ መመስከር ለቀይ ሽብር ገዳይ፣

ለርስዎ ሊሆን ቢችል የህሊና እርካታ፣

ምንም ባይተኩሱ ምን ባይስቡ ቃታ፣

ገዳይም ባንዳም ኖት የማታ የማታ !!

ሞትን ቀለም ቀብተው፣

ነጭና ቀይ ብለው፣

ለሞት ቁጥር ሰጥተው፣

ሲሉን ሰባት ነው፣

ክቡር ፕሮፌሰር፣

ማን እንደሚገደል ማን እንደሚታሰር፣

በጓዳ በር ገብተው ደርግን በማማከር፣

በየትኛው አይነት.... ሰው ቢሞት እርካታ፣

እንደምታገኙ እረፍት ወይ እፎይታ፣

የተሰለፋችሁ ከፋሽሽቶች ተርታ፣

ይኸኛው ይታሰር ይኸኛው ይፈታ፣



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

እነዚያን አትፍቱ እነዚያን ግደሉ፣

እነዚህን አጥፉ.... ትናንት እንዳላሉ፣

ዛሬ ንጹህ መስለው መድረክ ላይ ብቅ ያሉ፣

ሁሉም ተገድለዋል አንዳቸውም የሉ፣

ለወሬ ነጋሪ መስሎት ሰው ያልቀረ፣

ህሊናዎ እውነቱን እያውገረገረ፣

በክህደት ቁልቁለት አውርዶ ሲጥልዎ፣

በድሜዎ አይማሩም.... ቢሞቱም አፅምዎ !!

ክቡር ፕሮፌሰር ሞትን ቁጥር ሰጥተው፣

ሰባት ያደረሱት ደምረው ቀንሰው፣

ሞት ሰባት ሳይሆን ቅርጹ ዞሮ ዞሮ፣

አንድም የቁም ሞት ነው አንድም የተፈጠሮ::

በዚህ የሞት ስሌት፣

የርስዎን የድሜ ገመድ ቋጠሮ ቢፈቱት፣

ከተፈጥሮው በፊት በቁም ነው የሞቱት።

መትረየስ ሰው ሲያጭድ ምደሩ ጡር አፍርቶ፣

ጠርሙስ ሲከሰከስ ቀይ ቀለም ተሞልቶ፣

ብልት ሲሰነገል ባፈሙዝ ጥርስ ሲረግፍ፣

በነፈረ አካል ላይ ዘይት ሲርከፈከፍ፣

ጡቶች ሲቆረጡ ጠፍሮች ሲነቀሉ፣

ወጣቶች ተገድለው መንገድ ላይ ሲጣሉ፣

በሽቦ ክር ታንቀው ፖል ላይ ሲሰቀሉ፣

ነውሩ ባህል ሆኖ ሶዶም ሲከናወን፣



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

እሬሳ ሲሸቀጥ ለሃዘን ሲዘፈን፣

የደርጉ አማካሪ የለንደን ወያኔ፣

ሰልፍዎ ከማን ነበር ፕሮፌሰር ያኔ?

በለንደን ጉባኤ ዘጠና አንድ ግንቦት፣

ዋሽንግተን ሂልተን እምቢልታው የ“ክተት“

አዋጁን በይፋ…..ያሉን ፕሮፌሰር፣

ብትሄድ ኤርትራ ተገንጥላ ካገር፣

የኛ ናችሁ ስንል አይደለንም ብለው፣

ነጻ ወጣን ሲሉ ሰላሳ አመት ታግለው፣

ጎጆ እንውጣ ሲሉ መገንጠልን መርጠው፣

መቃዎም አያሻም እስኪመጡ ወደው፣

እኛ የኛ ናችሁ ስንላቸው ደፍረን፣

የናንተ አይደለንም ሲሉን እየሰማን፣

ስንቴ በልመና ዝምድና ይመጣል፣

የናንተ ነን ሲሉን መቀበል ይበልጣል፣

ያሉትን ዘንግተው በጠሩት ስብሰባ፣

ዛሬ ስለ አጋሜ ስለ ንግስት ሳባ፣

በባህል በታሪክ ድሮም በምብርትነት፣

ትግሬና ኤርትራ ለኢትዮጵያዊነት፣

ዳሩ መሃል ነበር ዛሬ ዳር የሆነው፣

ሲሉን ፕሮፌሰር ታሪኩን አዙረው፣

የድራማው ትርጉም ለገባው ሰው በውል፣

ተልእኮዬ ሰምሯል ማለትዎን ይረዳል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ሙያዎ አንድ ነገር ስልጠናዎ ሌላ፣

እንማማር ሲሉ ቧልት እንደተሟላ፣

ነውሩን ከበላ ሰው ከማያውቅ ይሉኝታ፣

ማን ከማን ምን ሊማር ከርስዎ ጋር ጨዋታ፣

ከቅጥረኛ ጋር ውል በወያኔ ጓሮ፣

ለማን ምን ሊፈይድ ባንዳ ተመካክሮ?

ጊዜ ክዶት ሲሄድ ሲጋለጥ ውሸቱ፣

የወይራ ጎባጣው ለቅኑው ጠላቱ፣

መጥረቢያ ይሆናል ከንጨት ጋር ተዋዶ፣

እንዲሉ ሆነና ግብርዎ ህዝብን ክዶ፣

ዱላ ሲሉዎት መላ ማጎንበስ ልማዶ፣

ዛሬም እንደ ጥንቱ ጎልቶ ባንዳነትዎ፣

በአለቀ እድሜ ዋሽተው ባዛውንትነትዎ፣

ለቀሪው ማፈሪያ ጽፈው ታሪክዎን፣

ለፍሪዳ ጥለው እናት አገርዎን፣

ከባንዳ ጋር ያውጡ የቁም ተዝካርዎን !!!



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com